# ምዕራፍ ስድስት

## ተጠራጣሪዎች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

1. ዮሐንስ ወንጌል ፩ ፣ ፫ «...አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ?» ይህን ማለቱ አማላጅነትሽን አልተቀበልኩም ማማለድ አትችይም ማለቱና አማላጅነትዋን መናቁ አይደለም ።

በዚህ ቤቃና ዘገሊላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምሩን እንዳደረገ ተገልጿል ። ነገር ግን ከዚያ በፊት ተአምር አላደረገም ማለት አይደለም ። ሥጋን ተዋህዶ ከተገለጸ በኋላ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተአምሩን ማድረጉን ሲገልጽ ነው እንደዚሁም ሁሉ በዚህ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ የእመቤታችን አማላጅነትዋ ይፋ የወጣበትና የታወቀበት ነው ።

ሠርግ ተጠርተው በሄዱበት ቤት የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ እመቤታችን ጠጅ አልቆባቸዋል እኮን አለችው ። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር አለ ። እመቤታችን የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል'ኮ ብላ ለጌታ መንገርዋ እርሱ የማያውቀው ነው ብላ አይደለም ። እርሱ የማያውቀው ነገር እንደሌለ ታውቃለች ። እንኳን ይኸን ግልጽ የሆነ ክስተት ቀርቶ ስውር የሆነውን ልቡና ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ሳይቀር እንደሚያውቅ እያወቀች ልክ ሌሎቹ ሰዎች ጌታን ደካማ ሰው አድርገው እንደሚወስዱት ሁሉ እ'ሰዋም አለማወቁን አውቃ አሳወቀችው ብሎ የሚያምን የሚያስተምር ቢኖር እጅግ የተሳሳተ ከመሆኑም አልፎ ጌታንም ሆነ እናቱን እንደመሳደብ ይቆጠርበታል ።

እርሱ የወይን ጠጅ እንዳለቀባቸው አውቆ ዝም ማለቱ የእርስዋ አማላጅነት እንዲታወቅ ስለፈለገ እርስዋ እንድትጠይቀው ብሎ ነው ። እርስዋም የወይን ጠጅ እንዳለቀባቸው እንደሚያውቅ እያወቀች አልቆባቸዋል'ኮ ብላ መናገርዋ የእርሱ ፈቃድ ጥያቄው (ልመ





www.ethiopianorthodox.org

ናው) ከእርስዋ እንዲመጣ ብሎ መሆኑን ስለተረዳችና ስለምታውቅ ነው ። እንዲህማ ባይሆን እመቤታችን የወለደችውን የልጅዋን ማንነት አላወቀችም ያሰኛል ። ነገር ግን ከእመቤታችን የተሰወረ ነገር አልነበረም ። (ሉቃ ፩ ፥ ፴፰) ሉቃ ፪ ፥ ፶፩)

ታዲያ ሁለቱ ተስማምተው ወይም በመንፈስ ተግባብተው ከሆነ ጥያቄውን ያቀረበችው ስለምን «አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ?» ሊላት ቻለ? የሚል ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር ምክንያቱንና የአባባሉን ትርጉም እንደሚከተለው እንደሆነ እንገልጽለታለን ።

አባባሉን አበክረን ስንመለከተው የነቀፋ ወይም አማላጅነትዋን ያለመቀበል ሳይሆን እንዳውም የፍቅር ፥ የትህትና የመቀበል መልስ ሆኖ እናገኘዋለን «እናቴ ሆይ ውሀውን ወይን ጠጅ አድርግላቸው ብለሽ ስትለምኝኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ምን ጸብ አለኝ? ከፍቅር በስተቀር ያልሽውን እፈጽምልሻለሁ ማለቱ ነው ። አባባሉ በዚህ መንፈስ መተርጐም እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ ፲፯ ቁ. ፲፰ መመልከት ይቻላል ። በዚህ ምዕራፍ ላይ ኤልያስን ትቀልብ የነበረች መበለት ልጅዋ ይታመምና ይሞትባታል ። በዚህን ጊዜ ሴትየዋ የሰማይን መስኮት ዝናም እንዳይሰጥ የዘጋ ምድር የዘሩባትን እንዳታበቅል የገዘተው ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይ በቤትዋ ከእርስዋ ጋር እያለ ልጅዋ መሞቱ አሳዝናአት «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን» አለችው ።

እንግዲህ ሴትዮዋ «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?» ማለትዋ ካንተ ጋር ጸብ አለኝ ወይ ላንተ ከመታዘዝ አንተን ከማስደሰት በስተቀር ያስከፋሁህ ነገር አለን? ማለትዋ መሆኑ ከማንኛችንም ሥውር አይደለም ። እንደዚሁም ሁሉ ጌታም «አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ ሲል? «እምቢ እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ጸብ አለኝ ወይ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል ። አንድም ውኃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትይኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ውኃውን ጠጅ ላላደርግላቸው ከሠርግ ቤት ተጠርቼ መጥቻለሁን ውኃውን ጠጅ ሳደርግላቸው ነው የመጣሁት (ታምራትን ልገልጽ ነው የመጣሁት) ሁሉም ነገር አስቀድሞ የተወሰነና በእርሱ ዘንድ የታቀደ መሆኑን ገለጸላት ።



«ነገር ግን ጊዜዬ አልደረሰም» ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ጊዜ ቦታ አለውና «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲል ።» በቀትር የሚሠራውን በሰልስት አይሠራውምና በሰለስት የሚሠራውን በነግህ አይሠራውምና ።

በተጨማሪም «ጊዜዬ አልደረሰም» ማለቱ ጠጁ ፈጽሞ አላለቀም ነበር ። ጠጁ ሳያልቅ በዚያው ላይ ውኃ አስጨምሮ ቢሆን ኖሮ ያለውን አበረከተው እንጂ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ አልቀየረም ብለው ምክንያት በደረደሩና ተአምራቱ ድንቅ ባልተባለም ነበር ። ስለዚህ ጠጁ ፈጽሞ እስኪያልቅ ጠብቂኝ ያን ጊዜ ታምራቴን አሳያለሁ በዚያን ጊዜ የአንቺም አማላጅነት የእኔም አምላክነት ይታወቃል ሲል ነው ። ሌላም ምክንያት ነበረው በዚያች ቅጽበት ይሁዳ ከሠርጉ ቤት ወጥቶ ስለነበር እርሱ እስኪመለስ ድረስ ጠብቂ ምክንያቱም እርሱ (ይሁዳ) በሌለበት ቦታ ተአምራቱን አድርጎ ቢሆን ኖሮ ከተአምራቱ ቢለየኝ በሞቱ ገባሁበት ብሎ ይህን ምክንያት አድርጎ በቀረበ ነበርና ጌታን ለመሸጥ ያነሳሳው ምክንያት እንደሌለ ምክንያት ለማሳጣት ።

እንግዲህ እመቤታችን የጠየቀችው አማላጅነትዋ በልጅዋ ዘንድ ተቀባይነትን እንዳገኘ ስላወቀች ለሰዎቹ «የሚላችሁን አድርጉ» ስትል ነግራቸዋለች ። ልመናዋ በጌታ ዘንድ ተቀባይነትን ባያገኝ ኖሮ አማላጅነቴን ነቅፎታል (አልተቀበለኝም) ብላ ዝም ብላ በተቀመጠች ነበር ። ዳሩ ግን ከላይ እንደተገለጸው የጌታ መልስ መልካምና አማላጅነትዋን መቀበሉን የሚገልጽ መሆኑን ስለተረዳች የሚላችሁን አድርጉ ብላለች ።

በተጨማሪም አማላጅነትዋን ጌታ እንደተቀበለው የሚያስገነዝበን ዝቅ ብሎ የጠየቀችውን መፈጸሙ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ ነው ።

ነገር ግን ይህን ሳያጤኑ ጌታን እንደ አንድ ተራ ስርዓተ አልበኛ ልጅ ቆጥሮ እናቱን በንቀት ከኔ ምን አለሽ? በሥራዬ ምን ያገባሻል ብሎ ዘልፏታል ብሎ መናገርና ማስተማር ጌታን ከመሳደብ አልፎ የስድብና የትዕቢት አስተማሪ አድርጎ ማቅረብ ነው ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን የጌታን ትሁትነት «ለእናቱ እየታዘዘ ማደጉን ነው» (ሉቃ. ፪ ፥ ፶፩) ። እርሱ እኛን እናትና አባታችሁን



www.ethiopianorthodox.org

አክብሩ እያለ እርሱ እናቱን «አንቺ ሴት በኔ ሥራ ምን አገባሽ ብሎ ተቆጣት ፣ ገለመጣት» ብሎ መናገር ጌታን ከአንድ ደካማ ሰው እሳ ንሶ ማየት ነው ። ጌታ ግን እንኳን ለእናቱ ለሰቀሉት ለአይሁድም የትዕቢት መልስ አልመለሰም «የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ማራቸው» ከማለት ሌላ ።

2. ዕብራውያን ፯ ፥ ፫ «መልከ ጼዴቅ አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም»

ይህን በመጥቀስ መልከጼዴቅ አባትና እናት እንደሌሉት እንደ መልአክ አድርገው የሚመለከቱት አሉ ። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ማለቱ ትውልዱና ነገዱ ከአብርሃም ወገን ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን ነውና ነገዱ። አይሁድ ሁሉ በትውልዳቸውና በነገዳቸው የሚመኩ ስለሆነ ወገኖቹን አይ ሁድን ደስ ለማሰኘት ብሎ እንደ ሆነ ነው እንጂ የመልከ ጼዴቅን ትወልድስ ታሪክ ጸሐፊዎች ግብጻውያን ዮሐንስ መደብርና አቡሻህር በ፩ኛው ክፍል ወልደ ንጉሠ ግብጽ ወኖባ ዘነግሠ በከነዓን ይለዋል የኖባና የግብጽ ንጉሥ ልጅ ማለት ነው ።

ኢየሩሳሌምን መጀመሪያ የቀረቀረና ያቀናት ሲዱ ይባላል ። እር ሱም የግብጽና የሱዳን ንጉሥ ነበር ይባላል ። ከግብጽም ተሻግሮ በከነዓናውያን ላይ በኃይል ነግሦባቸዋል ። በሀገሪቱም ላይ ከገሊላ ባሕር ዳር ከተማ ሠርቶ በስሙ ቤት ሳይዳ አሰኝቷታል (ቤተ ጸጋ ወሣህል) በዕብራይስጥ ቋንቋ የስጦታና የይቅርታ ቤት ማለት ነው ። (ዮሐ. ፫ ፥ ፳፫) ። ሲዱ ሳሌምን ይወልዳል ፣ በሳሌም ኢየሩሳሌም ተብ ላለች ። ሳሌም ሚልኪንና መልከጼዴቅን ይወልዳል ። መልከጼዴቅ ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ የእውነት ንጉሥ የእውነት ገዢ ማለት ነው ። እርሱም በቀራንዮ ላይ ቤተ መቅደስን አሠርቶ የደም መሥ ዋዕት ሳይሆን በኅብስት በወይን ሲሰዋበት ስለኖረ መልከጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን የእውነትና የሰላም ንጉሥ ተባለ በሚሙተ ክህነቱም አብርሃምን ባርኮታል ትውልዱም ከነገደ ከነዓን ነው ። አባትና እናቱም ከአሕዛብ ወገን ናቸው ።

ከመልከጼዴቅ እስከ ዳዊት ድረስ ሽህ ዘመን ከነዓናውያን ኢየሩሳሌምን ወርሰዋት ኑረዋል ። ከዚህ በኋላ ዳዊት በነገሠ በ፲ኛው ዓመት ዘርዓ ከነዓንን ነቅሎ ዘርዓ አብርሃምን ተክሎበታል ። በመጀ



መሪያ ዘመን በምድረ ከነዓን ከተማ የቀረቀረ የከነዓን ልጅ በኩሩ ሲዶን ይባላል ። የሲዶንም ልጆች በአባታቸው ስም ከተማይቱን ሠርተው ሲዶን ወይም ሲዶና ብለው ሰየምዋት ። ሁለተኛይቱን ግን ጢሮስ ብለው ሰየምዋት ይባላል ።

3. ፩ኛ ጢሞ ፪ ፥ ፭ እግዚአብሔር አንድ ነው ሲል በባሕርይ በመ ለኮት ሥላሴ አንድ መሆኑን ሲያስገነዝብ ሲሆን ፣ ሰው ሆኖ ሰውና እግዚአብሔርን ያስታረቀ ኢየሱስ ክርስቶስም አንድ ነው አለ ። በተለየ አካሉ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ መዋሐዱን ሲያስረዳ ነው ። ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስም ለሁሉ ቤዛ አድርጐ ራሱን አሳልፎ ለሕማም ለሞት መስጠቱን ገልጾ እርሱ ታርቆን በተለየ አካሉ ለአዳምና ለልጆቹ ሁሉ መስዋት ሆኖ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ህይወቱ ከመን ፈስ ቅዱስም ጋር እንዳስታረቀን ገለጸ ። እግዚአብሔርነት የሦስቱም ገንዘብ ነውና እግዚአብሔር የሚለው ስም የሥላሴ የአንድነት ስም ነው ።

ምናልባት አንድ ሰው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የሚለውን በአማላጅነት ወስዶት ዛሬም ከእግዚአብሔር አብ ጋር የምንገናኝበት አማላጃችን መሆኑን የሚያስረዳ ነው ሊል ይችል ይሆናል ። ይህ ግን ስሕተታዊ አመለካከት ከመሆኑ አልፎ የሥላሴን የባህርይ አንድነትና በመለኮታዊ ሥልጣን አንድ መሆናቸውን የሚ ጻረር ነው ። በእርግጥ ጌታችን ኢየስሱ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰ ቅሎ ስለ አዳም ካሣ ሆኖ መቅረቡ የማይካድ ቢሆንም የማስታረቅ አገልግሎቱ ግን የተፈጸመው በመስቀል ላይ ነው ። ከዚያ በኋላ ግን ሲያስታርቀን የሚኖረው በእለተ አርብ የፈጸመው የማስታረቅ አገል ግሎቱ ነው ። ይኸውም ተልዕኮ ለዘለዓለሙ ህያው እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን ፯ ፥ ፳፭ ላይ ገልጾታል «ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታር ቃቸዋል»

• መጽሔተ አሚን ገጽ 14—15



www.ethiopianorthodox.org

በዕለተ ዓርብ ባደረገው ተልዕኮ እስከ ምጽአት ድረስ ሲያድን በት የሚኖር ስለሆነ ያስታርቃቸዋል ሊል ቻለ እንጂ ዛሬም ክርስቶስ አብን ይለምናል ማለቱ አይደለም ። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት ሆኖ ምልጃን ይቀበላል ይማለዳል እንጂ አያማልድም ። በባህርይ በመለኮታዊ ሥልጣን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነውና ። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ከተባለ ታዲያ ክርስቶስ ለአብ የሚያማልደው ለምንድን ነው? ነገር ግን በዕለተ ዓርብ የፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ዛሬም እኛን ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ባጭሩ ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቀን ይኖራል እንጂ ዛሬ ኃጢአት ስንሠራ ከኃጢአታችን ለመንጻት የክርስቶስን ዳግመኛ መ ስቀል የምንጠባበቅ አይደለንም ። ይህንን ሁኔታ ግልጽ ሲያደርግ ጳው ሎስ ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል ብሎ ሕያው ዘለዓለማዊው አምላክ የፈጸመው የማስታረቅ ተልዕኮ ዘለ ዓለማዊ መሆኑን አስረገጠን እንጂ ክርስቶስ ዛሬም ያማልዳል አላ ለም ።

4. ዮሐ. ፲፱ ፥ ፴ «ጌታችን ኢየሱስም ሆምጣጣውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ» ተፈጸመ ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

፩ኛ/ በመጻሕፍት ይወርዳል ፥ ይወለዳል ፥ ይጠመቃል ፥ ዞሮ ያስተምራል በመጨረሻም ስለ ሁሉ ኃጢአት ተላልፎ ይሰጣል የተባለው በነቢያት የተነገረው ሁሉ እነሆ ደረሰ ተፈጸመ ማለቱ ሲሆን ፤

፪ኛ/ በማኅጸን የጀመረው ካሣ አሁን በዚች ሰዓት ተፈጸመ ብሎ ስለ አዳም ፍጹም ካሣ መክፈሉን መግለጹ ነው ።

5. ፩ኛ ዮሐ. መል. ፪ ፥ ፩ «ልጆቼ እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ፥ የበደለም ማንም ቢኖር ጰራቅሊጦስ አለን ከአባት ከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ቸር ነው ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ»

የዚህ መልእክት ዓላማ በድሎ ንስሐ የገባ ሰው ቢኖር ተስፋ ቆርጦ በበደል ላይ በደል በኃጢአት ላይ ኃጢአት እንዳይጨምር በሠራው የኃጢአት ሥራ ተጸጽቶ በደልኩ ብሎ ንስሐ እንዲገባ የሚመክር ሲሆን በኃጢአቱ ተጸጽቶ ንስሐ ለሚገባ ለዚያ ሰውም



ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የሚሰድልን ጰራቅሊጦስ አለን ከኃጢአታችን ያነጻናል ያድሰናል ። ጰራቅሊጦስ ማለት መንጽሒ ፥ (የሚያነጻ) መጽንዒ (የሚያጸና) መስተፍሥሒ ፥ (የሚያስደስት) መስተሥርይ ፥ ከሣቲ ፥ የሚገልጽ ናዛዚ (የሚያረጋጋ ማለት ነው ። ስለ ሆነም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ቸር የባሕርይ አምላክ ነው ። ብሎ የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ይመሰክራል እንጂ ክርስቶስ ጠበቃ ነው ከአብ ዘንድ ቀርቦ ስለ ኃጢአታችን ይሟገታል የሚል ቃል በፍጹም አልተጻፈም አግባባዊ አነጋገርም አይደለም ።

6. ፩ኛ ጢሞ ፬ ፥ ፩—፭ «መንፈስ ግን በግልጽ ይናገራል በኋላ ዘመን ብዙዎች ሃይማኖታቸውን እንደሚክዱ የሚያስቱ አጋንንትንና የሚያጠራጥረውን የሰይጣናትን ትምህርትም እንደሚከተሉ ሐሰትን የሚናገሩ በገዛ አሳባቸው የሚቃጠሉ ናቸው ። ጋብቻን እርም የሚሉ ምግቦችን የሚከለክሉ ጽድቅን የሚያውቁአት በልተው ያመሰግኑ ዘንድ እግዚአብሔር ለአማኞች የፈጠረውን «እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነውና ምንም የሚጣልም የለበትምና አመስግነው ከተቀበሉት በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ይቀደሳልና»

ይህን ቃል በሚገባ አንብበው ያልተረዱ አንዳንዶች በራሳቸው ትርጉምና አረዳድ በመውሰድ አንዳንዶች ምንኩስናን (ድንግልናን) ለመንቀፍ ነው ሲሉ ደግሞ ሁሉንም ፍጥረት እንድንበላ ተፈቅዷልና አይጡንም ማጐጡንም ፥ እባቡንም አህያውንም መብላት አለብን እንዲሁም ከቅጠላ ቅጠልም ጫት ፥ ሲጋራ የመሳሰሉት ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ስለሆኑ እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነውና የሚጣልም የለበትም ስላለ እኛም ጫት በመቃማችን ሲጋራ በማጤሳችን ልንወገዝ አይገባም ይላሉ ።

በመሠረቱ እግዚአብሔር የፈጠረው ሥነ—ፍጥረት ሁሉ ውብ ያማረ እንከን የማይወጣለት መሆኑ በሁላችንም ዘንድ የታመነ ሲሆን ነገር ግን «ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል» እንደሚባል ሁሉ ለምግበ ሥጋና ለምግበ ነፍስ የተፈጠረውን ለአንክሮ ለተዘክሮ የተፈጠረውን ለይቶ ማወቅና በየአግባቡ መጠቀም የሰዎች ሥራ ነው ። ለእንሰሳት የተሰጠውን ሣርና ቅጠል ሰው ቢበላ ከህመምና ከጉዳት በስተቀር የሚያተርፈው ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው ። እንዲሁም እባ



www.ethiopianorthodox.org

ብን ይዞ እስከነመርዙ ቢበላው መርዙ በመላ ሰውነቱ ተሠረጫጭቶ እንደሚገድለው እያወቀ ቢያደርገው ይህ ሰው የራሱ ገዳይ መሆኑ እንደሆነ ሊያጤነው ይገባል ።

የቅዱስ ጳውሎስ አገላለጽ ግን አንዳንድ የሐሰት መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለመንቀፍ ተብሎ የቀረበ ነው ። በዞራስተርን እምነት ለዚህ ዓለም ሁለት ፈጣሪዎች አሉ ። እነርሱም ደግ አምላክና ክፉ አምላክ ተብለው ይጠራሉ ። ደጉ አምላክ ወንድ ሲፈጥር ክፉው አምላክ ሴትን ፈጠረ ይላሉ ። እያይዘውም ከምግቦችም በደጉ አምላክ የተፈጠሩና በክፉው አምላክ የተፈጠሩ እንዳሉም ይገልጻሉ ። ስለዚህ የደጉ አምላክ ወገኖች ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ ደጉ አምላክ የፈጠራቸውን ብቻ መብላት አለባቸው እንዲሁም በክፉው አምላክ ከተፈጠሩት ከሴቶች ጋር መጋባት የለባቸውም ። ስለሆነም ጋብቻን ርኩስ ይሉ ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን እምነት ሲነቅፍ እንጂ እሱ ራሱ የመረጠውንና የያዘውን የድንግልና ህይወት መንቀፉ አይደለም ። (፩ኛ ቆሮ ፯ ፣ ፩—፯)

ቅዱስ ጋብቻም ሆነ የድንግልና ሕይወት ሁለቱም በአግባቡ ከተያዙ ለመንግሥተ ሰማያት ያበቃሉ ። ነገር ግን ከዚህ ወጥቶ ግቢ ርኩስ የሚል ቢኖር እርሱ ራሱ ርኩስ መሆኑን መግለጹ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል ። ምክንያቱም የተገኘው በጋብቻ ነውና ። እንዲሁም በድንግልና መኖርን (ሥርዓተ መላዕክትን) ንቆ ይህ አስፈላጊ አይደለም አያጸድቅም የሚል ቢኖር ይህም ሰው ምንም የማያውቅና መላዕክትን የጠላና የነቀፈ ቅዱሳንንም የጸረፈ መሆኑን ይረዳው ።

<u>መነናውያን ሦስት ሕግጋት ነበሯቸው ።</u>

1. አፍን መጠበቅ የመጀመሪያው ሕግ ነው «ማሕተመ አፍ ይባላል» (Signaculum Oris) በአንደበት ክፉና ነገረ ዘርቅ መናገር ክልክል ነው ሥጋ ጠጅና ወተት ዕንቁላልም አይቀመስም (በማናቸውም ቀን)

2. እጅን ከኃጢአት መጠበቅ «ማሕተመ ዕድ» (Signaculum Manum) እንስሳትን መግደል ዕጽዋት አዝርዕትን መቅጠፍ ፍሬ መልቀም ሳይቀር ክልክል ነው ።



3. በንጽሕና መጠበቅ «ማሕተመ ሕጽን» (Signaculum Sins) ጋብቻንና መራባትን ይከለክላል

ጳውሎስ የዚህን ዓይነት እምነት ሲነቅፍ እንጂ ጾምና ፣ ምንኩስናን ፣ የምንበላውን ለይተን ማወቅ እንደዚሁም ሰውነትን የሚጎዱትን ምግቦች መተው አግባብ አይደለም ማለቱ አይደለም ።

ምናልባት አንድ ሰው ሲጋራ ማጨስ ጫት መቃም ለምን ተከለከለ ብሎ ሊጠይቅ ይችል ይሆናል ።

በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል በቃል ሲጋራ አታጭስ ፣ ጫት አትቃም የሚል ባይኖርም ፤ በምሥጢር ወይም በትርጉም ማድረጉ አግባብ አለመሆኑን የሚጠቅስ አለ ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ናዝራውያን ሲጋራ የማይጨስበትን ምክንያት ሲገልጹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ (ቀን) የሌሎች ዕጽዋት ቅጠሎች ሁሉ ሲጠወልጉና ሲደርቁ የጥምባሆ (ሲጃራ) ቅጠል ለምልሞ ስለተገኘ ተወግዟል ይላሉ ። ይህ ግን በመጽሐፍም ሆነ በሊቃውንት ዘንድ የተደገፈ አይደለም ። እንዲሁም ሌሎች ደግሞ በአርዮስ ፈርስ ላይ የበቀለ ስለሆነ ነው የረከሰው ይላሉ ይህ ደግሞ ልዩ ክህደት ነው ። ምክንያቱም በዕለተ ሰሉሥ ያልተፈጠረ ሌላ ዕጽ በኋላ እንደ ተፈጠረ አድርጎ ማቅረብና ሌላ ፈጣሪ እንዳለ መናገር ስለሆነ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው ።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጥምባሆም ሆነ ሌሎች ጐጂ ዕጽዋትን መውሰድ (መጠቀም) ለምን በቤተ ክርስቲያን ተከለከለ የሚለውን ጥያቄ እንዲህ ይመልሱታል ።

፩. ሰውነትን የሚጎዳ ማንኛውም ቅጠላ ቅጠል የተፈጥሮ ባሕሪያችንና የጤና አጠባበቅ ደንባችን እንዳንጠቀም ይከለክለናል ። ስለዚህ ትምባሆ ሲቅሙት ወይም አመድ ቀላቅለው ሲጎርሱት ግማቱና ክርፋቱ መልካም አለመሆኑን ይገልጻል ። ሲጋራ አድርገው ሲመገምጉት ደግሞ ከጢሱ

---

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 67



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ተቀላቅሎ ልብንና ሳንባን እንዲሁም የአፍንጫ አስም ያለባቸውን ሰዎች እንደሚጐዳ አገር ያወቀው ጸሐይ የሞቀው እውነታ ስለሆነ ሰውነታችንን የሚጐዳ ነገር ደግሞ እንዳናደርግ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለታዘዝን ልንተወው ይገባል ፡፡

፮. መዐዛው ከቤተ ክርስቲያን ጢስ (ዕጣን) ጋር አይስማማምና በቤተክርስቲያን ውስጥ ማጤስና መቃም አያስፈልግም ፡፡ ቤተክርስቲያን ስንል ደግሞ ህንጻውን ብቻ ማለታችን እንዳልሆነ ከሁላችን የተሰወረ አይደለም ፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ስለሆነ ቤተክርስቲያን ነው ፡ (፩ኛ ቆሮ ፫ ፥ ፲፮ ፩ኛ ቆሮ. ፮ ፥ ፲፱) ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ማደሪያ በግማት በክርፋት ልናጥነው አይገባንም እግዚአብሔር ንጹሐ ባህርይ አምላክ ስለሆነ ንጹህ ነገር ይሻል ፡፡

፯. ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ የሚል መልእክት ጽፏል «ሌላው እናንተን አይቶ እንዳይስት ለራስህ የማትወደውን ለሌላ አታድርገው» ስለዚህ አንድ ክርስቲያን በዚህ ቃል መሠረት ወንድሙ ወይም ወዳጁ የማይወደው ጢስ የማይወደው ሽታ ስለሚሆን ስለወንድሙ ብሎ ይህን ጥሩ ሽታ የሌለውና ጐጂ የሆነን ነገር ይተወው ፤ (ሮሜ ፲፬ ፥ ፲፭—፳፩) ፡፡

7. መጽሐፈ መክብብ ፱. ቍ. ፬—፮ ፡፡ ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና ሰው ከሕያዋን ሁሉ ጋር በአንድነት ቢኖር ተስፋ አለው ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸው ም ተረስቷልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም በአንድነት ጠፍቶአል ከጸሐይ በታችም በሚሠራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም»

ይኸን ጥቅስ በመጥቀስ የሞቱ ጻድቃንና ሰማዕታት ሊያማልዱ አይችሉም የሚሉና ጥቅሱ ለሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት የተጠቀሰ እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ አሉ ፡፡



ነገሩ «ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ » አይነት ነው ፡፡ በእነዚህ ክፍሎች አተረጳጐም የልሞተ ውሻ» በሕይወተ ሥጋ ያሉ ኃጢአኛች ሲሆኑ የሞተ አንበሳ የተባሉት ደግሞ የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት ናቸው ፡፡ ይላሉ ሙታን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸውም ተረስቷልና ከዚያ በኋላ ዋጋ ያላቸውም የሚለውን ቃል ነቅሰው በማውጣት ጻድቃን ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ አንዳች አያውቁም መታሰብም የለባቸውም ከሞቱ በኋላ ዋጋ አይኖራቸውም ይላሉ ፡፡ ይኸ አባባል ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተያየት እጅግ የተሳሳተና ታላቅ ክህደት ሆኖ እናገኘዋለን ፡፡

## ሙታን አንዳች አያውቁም ሲባል እንዴት ነው

ሰው ማለት የሰባት ነገሮች ውሕደት ማለት ነው ፡፡ እነዚህም አራቱ ባሕርያተ ሥጋና ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ተብለው ይጠራሉ ፡፡ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ የሚባሉት እሳት ፤ ነፋስ ፤ መሬት ፤ ውኃ ሲሆኑ ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የሚባሉት ደግሞ ለባዊነት (ልብ ማድረግ ማወቅ ፤ (ነባቢነት (መናገር) ፤ ሕያውነት (ሕያው መሆን) ናቸው ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ሰው የሥጋና የነፍስ ውሕደት ነው ፡፡ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ነፍስና ሥጋው በተዋሕዶ ሆነው ያንቀሳቅሱታል ዕለተ ሞቱ ደርሶ ወደ ላዕላዊው ፈራጅ ሲጠራ ተዋሕደው ይኖሩ የነበሩት ነፍስና ሥጋው በሞት አማካይነት ይለያያሉ ፡፡ ነፍስ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ባሕርይዋ ህያውነት ስለሆነ ለፍርድ ወደ ህያው አምላክ ስትሔድ ሥጋ ግን ወደ መቃብር ይወርዳል ፡፡ ወደ አፈርነቱ ይመለሳል ፡፡ ሕያዊት ነፍስ ተዋሕዳው በነበረ ጊዜ ይፈራ ይከበር ፤ ያውቅ የነበረው ሥጋ አሁን ግን ነፍስ በተለየችው ጊዜ አስከሬን ይሆናል ክብሩን ሁሉ ይገፈፋል እንደ ቆሻሻ ይቆጠራል ሬሳ ተብሎ እንደ እንሰሳት ሬሳ ይጣላል ክብርም አይይኖረውም ቀደም እንደ አንበሳ ግርማው ያስፈራ ያስደነግጥ የነበረው ከሞተ በኋላ ግን በሕይወተ ሥጋ ያሉ እንደ ውሻ የተናቁ ሰዎች በእግራቸው ይጠቀጥቁታል ፡፡ ይኸ ሁሉ ግን በአጠቃላይ ሰው ለተባለ ሁሉ የሥጋውን ፈራሽ በስባሽነት ለማስረዳት የተነገረ እንጂ ለጻድቃን ሰማዕታት ተለይቶ የተነገረ አይደለም በአንጻሩ ደግሞ ሰው ሁሉ በሥጋው በኩል እንዲህ አይነት አነጋገር ቢነገርለትም በነፍስ በኩል ስላለው ሕያውነት ደግሞ በሰማይ በእግዚአብሔር ገነት ወይም በሲኦል



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበን ሀቅ ነው ። ሉቃ. ፳፫ ቊ. ፵፫ ። ራዕይ ፮. ቊ. ፱ ። ሉቃ. ፲፮. ቊ. ፲፱—፴፩ ።

ሙታን አንዳች አያውቁም የሚለው አባባል በሥጋቸው እንጂ በነፍሳቸው አለመሆኑን ልናውቅ ይገባናል ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል «በቃለ እግዚአብሔር ስላመኑ ሕጉን ስለ ጠበቁ በሰማዕትነት የሞቱ ሰዎች ነፍሳቸውን ከመሠዊያ በታች አየሁ» ራእይ ፮. ቊ. ፱ ። ሥጋቸው በምድር ላይ በውስተ መቃብር ሲሆን ሕያዊት ነፍሳቸው ግን በእግዚአብሔር እጅ መሆንዋን ይነግረናል» የጻድቃን ነፍሳቸው በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነው» እንደተባለው ሁሉ ጻድቃን ሰማዕታት ነፍሳቸውን ለታመነው አምላካቸው ይሰጣሉና «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጣራ ይወግሩት ነበር» ሐዋር. ሥራ ፯. ቊ. ፶፱ ። አምን በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ነፍስ በጌታ እጅ ውስጥ ነው የምትሆነው ።

ስለዚህ በሥጋ ቢሞቱም በነፍስ ግን ሕያዋን ናቸው ። «የሕያዋኑ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም» ማርቆስ ፲፪. ቊ. ፳፯ ። እንግዲህ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ በሥጋ ሞተው መቃብራቸው የታወቀ ሲሆን ፤

ጌታ ግን የእነዚህን የሞቱ ጻድቃን ስም ጠርቶ ሕያዋን ናቸው ማለቱ የሞቱት በሥጋ እንጂ በነፍስ ሕያዋን መሆናቸውን ለማሳወቅ አይደለም ?

## ለሞቱ ጻድቃንና ሰማዕታት መታሰቢያ ማድረግ በረከት እንደሚያሰጥ

መታሰቢያቸው ተረስቷልና የሚለውን በመጥቀስ የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትን ማዘከር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ አሉ ዳሩ ግን ይኽ አባባል ስለ ክርስቶስ ወንጌል ሲሉ ሰውነታቸውን ለእሳት ለስለት አሳልፈው ለሰጡ ለወንጌል አርበኞች ለጻድቃን ሰማዕታት የተነገረ አለመሆኑን በሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እናረጋግጣለን ፤



ታላቁ የጥበብ ሰው ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ም. ፲. ቊ. ፯ ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው የኃጥአን ስም ግን ይጠፋል» እንግዲህ ይኸን ቃል መነሻ አድርገው የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትን መታሰቢያ የሚያደርጉ ሰዎች ከሞቱት ጻድቃን ሰማዕታት በረከትን ለመቋደስ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ፤

ልበ አምላክ ዳዊት ደግሞ ጻድቃን ሰማዕታት እንደተቃዋሚ (ተጠራጣሪዎቹ) አባባል ሞተው ፈርሰው በሰብሰው የቀሩና መታሰቢያቸውም በምድር ባሉ በክርስቶሳውያን ዘንድ የተዘነጋ ሳይሆን ለዘላለም እንደሚኖር ሲገልጽ «የጽድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል» ሲል ዘግቧል መዝ ፻፲፩/፻፲፪/ ቊ. ፮ ፤

ይኸው ነቢይ እግዚአብሔር ዳዊት እግዚአብሔር ለጻድቃን በሕይወተ ሥጋ እያሉ የገባላቸው ቃል ኪዳን ከሞቱ በኋላም እንደሚሠራ ሲገልጽ «ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል» ብሏል መዝ. ፻፲ (፻፲፩). ቊ. ፭ ።

ሌላው የእግዚአብሔር ነብይ የሆነው ኢሳይያስ ደግሞ እግዚአብሔር በእውነት ለሚያመልኩት ሰዎች የሰጠውን ጸጋ ሲያስገነዝብ ፤

እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና በቤቴና በቅጥሬ (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ» ኢሳይ ፶፮. ቊ. ፬—፭ ።

እንግዲህ ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱሳን በከፊል ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ የምትቀበል ስለሆነች ይኸን የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ላይ አውላዋለች ። ለዘሁም ሁነኛ ማስረጃዎች ለእግዚአብሔር ቃል ሲሉ በሰማዕትነት ባለፉት ጻድቃን ስም ቤተክርስቲያን ማሳነጽዋ ነው ። ቤተክርስቲያን ክቡርና ልዑል እግዚአብሔር የሚሠለስባት የሚቀደስባት ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባት ሲሆን ዳሩ ግን ቅዱሳኑ ይታሰቡበታል ። ለዚሁም እንደ አብነት አድር



www.ethiopianorthodox.org

ግን በጳውሎስና በጴጥሮስ ስም የተሰየሙትን ቤተ ክርስቲያኖች ልንጠቅስ እንችላለን ።

እግዚአብሔር ለስሙ ፥ ለክብሩ ለአምልኮቱ ቀንተው በስማዕትነት ያለፉትም ሆኑ በሕጉ በትዕዛዙ ጸንተው የኖሩ ሰዎች የማይጠፋ የዘላለም ስም እንደሰጣቸው ገልጾአል በዚህ ምክንያት የተነሣ ኢሳይያስም ሆነ ዳዊት ከሞቱ ረዥም ጊዜ ቢሆናቸውም ዳሩ ግን ጌታ እግዚአብሔር ስማቸው እንደማይጠፋ ስለተናገረ እርሱን በሚያመልኩት ሰዎች ዘንድ ሁሉ ሲታሰቡ ይኖራሉ ።

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ ወን. ም. ፲ ቍ. ፵፪ ላይ እንዲህ ሲል ተናግሯል «ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም» በማለት ዛሬ ክርስቲያኖች በሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት ስም የሚያደርጉትን ዝክር (መታሰቢያ) በእውነት ተቀብሎ ለአድራጊዎቹ ዋጋ እንደሚሰጣቸው በማይታበል ቃሉ ተናግሯል እንግዲህ ከጌታ የበለጠ ማን ሊያረጋግጥልን ይችላል ።

## ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም የሚለው አባባል ሰሞቱት ጻድቃን ሰማዕታት የሚስማማ አባባል ነው?

እንደ እውነቱ ከሆነ ጻድቃን ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም የሚለው አባባል በክርስቶስ አዳኝነት አምናለሁ ከሚል ክርስቲያን አፍ ይወጣል ተብሎ ሊታመን አይችልም ። ምክንያቱ እነዚያ ስለ እግዚአብሔር ቃል የተወደደ መሥዋዕት ሆነው ያለፉ ሰማዕታት ዋጋቸው ፈርሶ በስብሶ ሙቅረት ወይም ዋጋ ቢስ መሆን ከሆነ ዛሬ በ21ኛው ሙቶ ክፍለ ዘመን ያለን የክርስቶስ አማኞችስ ተስፋችን ምንድር ነው ? እነዚያ ስለተጋደሉአቸው ዋጋ ካልተሰጣቸውና ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም ከተባለ እኛስ ምን ዓይነት ዋጋ ለማግኘት ከዚች ክፉ ዓለም ከሰይጣን ጋር እንታገላለን ።

በመሠረቱ ይኸ አባባል የእግዚአብሔር ቅዱሳንን መድፈር ብቻ ሳይሆን ዛሬም በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን ዘላለማዊ ዋጋ በተስፋ



የምንጠባበቀውን ሁሉ ተስፋ የሚያስቆርጥና ወደ ኃጢአት እንድንመራ ተስፋ መንግሥተ ሰማይን እንዳናዘክር በሰይጣን በኩል የተጣለ የማሰናከያ መረብ ነው ።

እውነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነችው መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ስለሚያምኑ ሰዎች ተስፋ ሲናገር እጠቅሳለሁ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» ዮሐ. ወን. ፲፩. ቍ. ፳፭ ።

እንግዲህ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት ከጉስቁልና ወደ ፍጹም ደስታ ከዋጋ ቢስነት ወደ ዋጋ ማግኘት መሸጋገሩን ገልጾልናል ። ታዲያ እውነተኛው ጌታ በእርሱ የሚያምኑ ዘላለማዊ ዋጋ እንደሚያገኙ እየተናገረ ጻድቃን ሰማዕታት ከሞት በኋላ ዋጋ የላቸውም ብሎ መናገር አግባባዊነት አለው? የዚህ አይነት እምነት ያላቸው ሰዎች ቁጥራቸው ከክርስቶሳውያን ሳይሆን ከሰዱቃውያን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል «ሰዱቃውያን ሰው ከሞት በኋላ ዋጋ የለውም የሚሉ ናቸውና» ሐዋ/ሥራ ፳፫. ቍ. ፰ ።

ክርስቶሳውያን ግን መሪያቸውና ፈጣሪያቸው ልዑል ባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን መሠረት በማድረግ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ዋጋ እንዳለውና ዋጋውም ዘላለማዊ ሕይወት መሆኑን ያምናሉ ያስተምራሉ ።

በመጽሐፈ ምሳሌ በም. ፲ በቍ. ፳፭ ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን «ዐውሎ ነፋስ ሲያልፍ ኃጥእ አይገኝም ጻድቅ ግን የዘላለም መሠረት ነው» ከዚህ አባባል የምንረዳው ቁም ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ያመነ ሰው ዘላለማዊ ዋጋን በማግኘት ለዘላለም ከአምላኩ ጋር በፍስሐ እንደሚኖር ነው ።

የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት አስከሬን ዋጋ የለውም ተብሎ እንደ አልባሌ ነገር መታየት የለበትም ኃይለ እግዚአብሔር የሚገልጥበት ነውና ። ለዚሁም ዓቢይ ምሳሌነት የሚኖረው የኤልሳዕ አጥንት ነው ። ከሞት እጅግ ብዙ ጊዜ የሆነው ነቢዩ ኤልሳዕ በአጽሙ የሞተ ሳው እንዳስነሳ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ም. ፲፫ በቍ. ፳፩ ላይ ሰፍሯል ።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ የእግዚአብሔር ኃይሉ በሕይወተ ሥጋ ባለ ኃጥእ ሰው ላይ ሳይሆን በሞተው ጻድቅ ላይ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ስለገለጸልን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም በሕይወተ ሥጋ ያለኃጥእ ይበልጣቸዋል ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የእግዚአ ብሔር ቅዱሳንን ለመሳደብ ተብሎ መሆኑን መረዳት አለብን ።

የሙክብብ አባባል ሰው ከሞተ በኋላ በሥጋው በኩል የሚገጥመውን ሁኔታ ለመናገር ፈልጐ እንጂ እንደተጠራጣሪዎች አባባል የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት አያማልዱም ለማለትና ከሞቱ በኋላ የሚሆነውን ነገር አያውቁም ለማለት አይደለም ። በሕየወተ ሥጋ እያሉ ከሥጋ ጋር እየተሟገቱ ጸጋ እግዚአብሔር ከእነርሱ እንዳልተለያቸውና ልቡና ያሰበውን በስውር ሰዎች ያደርጉትን ድርጊት ያውቁ እንደነበረ በወንጌል ላይ የተገለጸ ነው ። ሐዋ. ሥራ. ፳፫ ቍ. ፲፪—፳፪ ።

በሕይወተ ሥጋ እያሉ ታላቅ ሙግት እንደሚኖር ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው ክታቡ ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል «ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ ። ብልቶቻችሁ ዓመጻ ሊያደርጉ ለርኩስነትና ለዓመጻ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንደቀረባችሁ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ እንዲቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አቅርቡ» ሮሜ. ፮ ቍ. ፲፱ ። እንዲሁም» ሕግ መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አድርጋለሁ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደሆነ እመሰክራለሁ እንደዚህ ክሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና» ሮሜ ፯ ቍ. ፲፬—፲፰ ።

ከላይ ጳውሎስ የገለጸው ሥጋ ምን ያህል ለክርስቶስ ወንጌል እንዳንገዛ ተጽእኖ እንደሚያደርግብን ነው ። ግን ይኸን ሥጋችንን ተሟግተን ድል በማድረግ በእግዚአብሔር ጸጋ እንቃኛለን ዳሩ ግን ይኸ ሥጋ ሙግቱን አያቆምም ። አንዳንድ ጊዜ ለኃጢአት ሲያንበረክከን ይታያል በንስሐ ግን እንመለሳለን ።



እንግዲህ ምን እንላለን በሥጋችን የኃጢአት ባሪያ በምንሆን በት ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ከተጥለቀለቅን ሩጫችንን በድል አድራጊነት ከፈጸምን በኋላ ይኸን ጸጋ እግዚአብሔር ይቀነስብናል? እንግዲህ ካልተቀነሰብን በሕይወተ ሥጋ እያሉ ቅዱሳን በተሰጣቸው ጸጋ ያማልዱ እንደነበር ሁሉ ይኸን ጸጋቸው አሁንም ስላልተነጠቃቸው በእግዚአብሔር ዘንድ በአጸደነፍስ ሆነውም ስለ እኛ ማማለድ ይችላሉ አይችሉም የሚል ካለ ግን ለምን? ምን ያግዳቸዋል? የሚል ጥያቄ እናቀርባለን ።

ሞት ማለት ለቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ከመኖር ይልቅ እጅግ የሚሻል ጸጋ ከጌታቸው የሚያገኙበት ነውና «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው» ፊልጵ ፩ ቍ. ፳፫ ። በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ መሆኑን ተናግሯል ፡

8. <u>፪ኛ ቆሮ. ፫. ቍ. ፯—፲፩</u> ። ያለው ማብራሪያ እንደሚከተለው ነው ። «ስለዚያ ስለተሻረው ስለ ፊቱ ክብር» የሚለውን በመጥቀስ ሕገ ኦሪት ተሽሯልና ዛሬ ሊፈጸም አይገባውም ስለ ዚህም ታቦትም ሆነ ቤተ መቅደስ አያስፈልግም የሚሉ አሉ ። ዳሩ ግን ጳውሎስ ሕገ ኦሪት ተሽራለችና ከእንግዲህ ወዲህ ሕግንና ነቢያትን መቀበል የለብንም ማለቱ አይደለም ሕግና ነቢያትማ ሊሻሩ እንደማይችሉ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ ሕግና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ» ማቴ. ፭ ቍ. ፲፯ ። በማለት ሕገ ኦሪትን ፍጽምት ሕግ ሊያደርግ መምጣቱን ተናግሯል ።

ስለዚህ ጳውሎስ ጌታ ያልሻራትን ሕገ ኦሪት እርሱ ሊሽርና ሊያጠፋ አይችልም ጳውሎስ ለወንጌል ምሳሌ የሆነችው ኦሪት ክብር ይደረግላት እንደነበር ጠቅሶ ያቺ ለወንጌል ምሳሌ ጥላ ሆና የነበረችው ሕገ ኦሪት እንደዚያ አይነት ክብር ከተሰጣት አማናዊዋ ሕግ ሕገ ወንጌልማ ምን ያህል አትከብር ።እንዲሁም በሙሴ ፊት ላይ ዘላለማዊ ያልሆነ ጊዜያዊ ብርሃን (የተሻረ) ወይም ኃላፊ ብርሃን ስለተሣለባት



www.ethiopianorthodox.org

እስራኤል የሙሴን ፊት ማየት የማይቻላቸው እስኪኾኑ ድረስ ክብር ከተደረገለት/ሙሴ ፊትህን ሸፍንልን ብለውት ነበር ።

መንፈስ ቅዱስ ለጸፉት ሕግ (በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተቃኝተው የጸፉዋት በመሆንዋ ነው ። ) ለወንጌልማ ምን ያህል ክብር ይደረግ ላት ይኾን ሞትን ለምታስፈርድ ኃጢአትን ቆጥራ ቆጥራ ለምትናገር ለዚያች ለሕገ ኦሪት ብዙ ክብር ከተደረገላት ሕይወት የሚገኝባት ሕገ ጽድቅ ወንጌልማ (በኦሪት ሕግ የሰው ልጅ ፍጹም ድህነት አላ ገኘም በክርስቶስ ካሣ ግን ፍጹም ድህነት ተገኝቷል እግዚአብሔ ርና ሰውን ለይቶ የነበረው የኃጢአት ግድግዳ ፈርሷል የተዘጋችው ገነት ተከፍታለች ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በምላት ተሰጥቷል ለዚህ ነው ሕገ ጽድቅ የተባለችው ።

ምን ያህል ትከብር ይኾን በማለት ሕገ ወንጌልን ከሕገ ኦሪት እያነጻጸረ ነው የመጣው በዚህ ፍጹም ክብር ባነጻጸራት ጊዜ ከብራ የነበረች ሕገ ኦሪት እንዳልከበረች እስከትሆን ደረሰች ። ከወንጌል ጋር አነጻጽሮ የወንጌል ክብር ፍጹም መሆኑን ሲያሳይ እንጂ ኦሪት የከበረች አይደለችም ማለት አይደለም ።

እንግዲህ አለ ጳውሎስ በምሳሌነት (በጥላ) የነበረው የኦሪት ሕግ ክብር ካገኘ ባለማለፍ ጸንቶ የሚኖረው ሕገ ወንጌልማ ምን ያህል ይከበር ይኾን እንዲሁም ኃላፊ (ምሳሌ) የሆነውን ሕገ ኦሪትን የያዘ ክብር ካገኘ (ሙሴ) ባለማለፍ ጸንቶ የሚኖር ሕገ ወንጌልንማ የያዘ ምን ያህል ክብርን ያገኝ ይሆን በማለት በወንጌል በማመን የሚገኘውን ፍጹም ክብር ገለጸ እንጂ ሕግና ነብያትን አትቀበሉ አላለም ።

ስለሆነም ዛሬ ጥንታዊትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ሕግንና ነቢያትን ከሐዋርያት ትምህርት ጋር በማጣጣም ፍጹም የሆነውን የጌ ታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ ትፈጽማለች ። ሕግንና ኦሪትን ሊሽር የመጣ ሳይሆን ፍጹም ሊያደርግ የመጣውን አምላክ ከነቃሉ ተቀብላ ያመነች ናትና ።

9. <u>ትንቢተ ኢሳይያስ ፩. ቊ. ፲፫</u> «...ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ <u>ዕጣን በእኔ ዘንድ አስጸያፊ ነው</u> መባችሁንና ሰንበታችሁን በጉባኤም መሰብሰባችሁን አልወድድም» በኢሳይ



ያስ አድሮ ዕጣን በእርሱ ዘንድ አስጸያፊ መሆኑን ተናግሮ ሳለ በኦር ቶዶክስ ቤተክርስቲያን የዕጣን መስዋእት ለምን ይቀርባል የሚል ጥያቄ የሚጠይቁ አሉ ።

በመሠረቱ እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ የዕጣን መስዋእት ጨርሶ አታቅርቡ አልወድም ያለበት ጊዜ የለም በኢሳይያስ አድሮ የተናገረውን በጥንቃቄና በጥሞና ስናስተውለው ሐሳቡ ተጠራጣሪ ዎች ከተረዱት ውጭ ሆኖ እናገኘዋለን ።

እሥራኤል የእግዚአብሔርን ሕግና ቃል ሳይፈጽሙ የሚቃጠል የአውራ በግ መሥዋዕትንና የፍሪዳን ስብ እንዲሁም የዕጣን መስዋ ዕት ይዘው በቤተ መቅደስ ያቀርቡ ነበር ዳሩ ግን የሠራዊት ጌታ እግ ዚአብሔር ከላይ የተጠቀሱትን መስዋእት ከማምጣታቸው በፊት መጀመሪያ የራሳቸውን ሕይወት መስዋዕት አድርገው ማቅረብ እንደ ሚገባቸው ልባቸው ከእግዚአብሔር ርቆ ገንዘባቸውን ወደ ቤተ መቅደስ ቢያመጡ እግዚአብሔር በመስዋዕታቸው ተደሳች እንዳል ሆነ ይገልጻል ። ይኸንንም ለማወቅ ቁጥር ፲፮ እና ፲፯ ብንመለከት «ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ ክፉ ማድረግን ተው መልካም መሥራትን ተማሩ ፍርድን ፈልጉ የተገፋውን አድኑ ለድሀ አደጉ ፍረዱለት ስለ መበለቲቱም ተሟገቱ» በማለት መስዋዕቱን ከማቅረባቸው በፊት ሊያደርጉ የሚ ገባቸውን ቅድመ ዝግጅት ገልጾላቸዋል ። እንግዲህ ከፍ ብሎ መነሻ ውን ዝቅ ብሎ መቋጫውን ሳይመለከቱ አንድ ሐረግ መዞ በማውጣት ወደ ስህተት ገደል ተወርውሮ ከመውደቅ ምዕራፉን በሙሉ ማንበቡ ይመረጣል ።

ደግሞም እግዚአብሔር በኃጢአት ሥራ ተሞልታችሁ ያመጣ ችሁልኝ ዕጣናችሁ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም አለ እንጂ ዕጣን የተመረጠ መሥዋዕት ነው አላለም ይኸም ይታወቅ ዘንድ በኦሪት ዘጸአት ም. ፴ ቍ. ፴፬—፴፰ ባለው ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ እን ዲህ ብሎታል «ጥሩም ዕጣን ውሰድ ... በጨው የተቀመመ ንጹሕና ቅዱስ አድርገው ... እንደእርሱ የተሠራ ዕጣን ለእናንተ አታድርጉ በእናንተም ዘንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ሊያሸተተውም እንደ እርሱ የሚያደርግ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ ።

እግዚአብሔር የዕጣን መስዋዕት ለእርሱ የተቀደሰና የተመረጠ እንደሆነ መናገሩን ልብ አልን?



www.ethiopianorthodox.org

መልካም መዓዛ ያለው መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀ ባይነት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል «እግዚአብሔርም መል ካሙን መዓዛ አሸተተ...» ኖኅ ያቀረበውን መስዋዕትና ልመናም ተቀበለ ። ዘፍ. ፰ ቍ. ፳፩ ።

በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበው ለእግዚአብሔር መልካም ሽታ ያለውን የዕጣን መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበር በተለ ያየ ሥፍራ እናገኛለን ዛሌ ፩. ቍ. ፲፫ ።

ይኸ ሥርዓት ባንድ ወቅት በተወሰነ ክልል ብቻ የሚደረግ ሣይ ሆን እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታ ሁሉ እንደሚሆን አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢዩ ሚልክያስ አንደበት አስነግሯል «ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ ። » ትን. ሚል ፩ ቍ. ፲፩ ።

የዕጣን ስጦታ (ገጸ በረከት) እግዚአብሔርን የሚያስደስተው መሆኑን የተረዱት የጥበብ ሰዎች ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ካመጡለት ገጸ በረከት አንዱ ዕጣን ነው ማቴ. ፪ ቍ. ፲፩ ። ይኸውም ዘላለማዊ ክህነቱን መለኮታዊ ማዕዛውን ለማመልከት ነው ።

የዕጣን መስዋዕት ማቅረብ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እግዚአብሔርንም ፍጹም የሚያስደስተው መሆኑን ዮሐንስ በራእዩ የተመለከተው እው ነታ ነው ። «በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው ። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ» ራእይ ፰. ቍ. ፬ ። ራእዩ ፭. ቍ. ፰ ።

ቤተ ክርስቲያናችን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ዕጣን የምታጥነው የቀ ረበው ጸሎት ልመና በእግዚአብሔር ፊት እንዲደርስ ነው ። ሕጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ መሆኑን ከላይ ጠቅሰናል ።

አንዳንድ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ዕጣን ቤታቸው ቡና አፍልተው በአምልኮት መልክ ሲያጨሱ ይታያሉ እነዚህ ሰዎች ፍጹም የተሣሣቱና ከእግዚአብሔር ሕግ የወጡ መሆናቸውን ሊያውቁ ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org